# መረጃ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
2009/35A
Tel. (011) 517-4007 Fax. (011) 124-2454
ለተ□ ማሪ መረ□ : 011-517-4308.
የኢንተርኔት አድራሻ: http://ethiopia.usembassy.gov

---

# ‘ዲቪ’ 2011

# እ ን ዳ ይ ታ ለ ሉ!!

## የ‘ዲቪ’ ዕጣ የወጣላቸው ሰዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ እውነቶች!

(አዲስ አበባ የሚገኘው) የአሜሪካ ኤምባሲ ከዚህ በታች የሰፈሩትን ቁም ነገሮች በውል እንድታውቋቸው ይፈልጋል፦

**የዳይቨርሲቲ ቪዛቸውን ለማግኘት አዲስ አበባ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ማመልከቻ ማስገባት የሚሹ የዲቪ ዕጣ አሸናፊዎች በሙሉ ከዚህ በታች የሰፈሩትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል። እነዚህን መመዘኛዎች የማያሟሉ የዲቪ (ዕጣ) አሸናፊዎች ቪዛ አይሰጣቸውም። አንድ የቪዛ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው በአሜሪካ የቆንስላ ሠራተኛ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገለት በኋላ፣ የአሜሪካ ኤምባሲ የከፈለውን ገንዘብ ተመላሽ ለማድረግ ምንም ስልጣን የለውም። ቪዛ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርቡ የዲቪ አሸናፊዎች በሙሉ ከዚህ በታች የሰፈሩትን የመመዘኛ ነጥቦች ልብ እንዲሏቸው የአሜሪካ ኤምባሲ ያሳስባል።**

- <u>(የቪዛ) ማመልከቻ</u>፦ የቪዛ ማመልከቻ ከአንድ ጊዜ በላይ አያስገቡ። ከአንድ ጊዜ በላይ ማስገባትዎ ከተደረሰበት የቪዛ ማመልከቻዎ ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል። ስለዚህ አንድ ጊዜ ብቻ ያመልክቱ።

- <u>ማመልከቻ/ፎቶግራፎች</u>፦ ለእርስዎ ማመልከቻ ተጠሪው እርስዎና እርስዎ ብቻ ነዎት። በማመልከቻዎ ላይ ያሰፈሯቸው ስሞች፣ መረጃዎች፣ ወይም ፎቶግራፎች የተሳሳቱ ከሆነ የቪዛ ማመልከቻዎ ውድቅ ይሆናል።

- <u>መረጣ</u>፦ የዲቪ ዕጣ የወጣልዎት መሆኑን የሚገልፀው የ‘እንኳን ደስ ያለዎ’ ደብዳቤ፣ ለቪዛ ቃለ-መጠይቅ ለመቅረብዎ ዋስትና አይሆንም። ለቪዛ ቃለ-መጠይቅ እንደሚቀርቡ እርግጠኛ የሚሆኑት ከሌላ ከማንም ሳይሆን ከአሜሪካ መንግሥት የተላከ የቃለ-መጠይቅ ቀነ-ቀጠሮዎትን የሚያሳውቅ ደብዳቤ በፖስታ አድራሻዎ ሲደርስዎት

ብቻ ነው። የቪዛ ማመልከቻዎ ሒደት ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ምንም ዓይነት የጉዞ እቅድ አያውጡ።

- <u>ክፍያዎች</u>:- የዲቪ ሎተሪ ማመልከቻ ለመሙላት ምንም ዓይነት ክፍያ አያስፈልግም። የዲቪ ማመልከቻ ለማስገባትም ሆነ ማመልከቻውን ለመሙላት ወኪል ወይም ጠበቃ አያስፈልግዎትም። የዲቪ ሎተሪ አሸናፊዎች ጉዳያቸው በሒደት ላይ ሳለ ክፍያ የሚፈፅሙት ለአሜሪካ ኤምባሲ ብቻ ነው። **ለአሜሪካ ኤምባሲ ካልሆነ በቀር ለማንም ክፍያ እንዳይፈፅሙ።**

- <u>ስፖንሰር</u>:- **ለዲቪ ብቁ ለመሆን የዩናይትድ ስቴትስ -አልያም የሌላ (አገር)- ስፖንሰር አያስፈልግዎትም።**

- <u>ጋብቻ</u>:- የዳይቨርሲቲ ቪዛ ለማግኘት የግድ ባለትዳር መሆን የለብዎትም (አይጠበቅብዎትም።) በምንም ምክንያት፥ ሐሰተኛ ትዳር ምስረታ ውስጥ አይግቡ። **በሐሰት የትዳር ግንኙነት የመሰረቱ መስለው መቅረብ ቀሪ እድሜዎን ሙሉ ወደ አሜሪካ የመጓዝ ዕድል ያሳጣዎታል።**

- <u>ቤተሰብ</u>:- የዲቪ ቪዛ ማመልከቻዎን በሚያስገቡበት ጊዜ በማመልከቻዎ ላይ ባለቤትዎን እና እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ያላገቡ ልጆችዎን በሙሉ አለማካተት የዲቪ ቪዛ ጥያቄዎ ተቀባይነት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል።

- <u>ትምህርት</u>:- ለዲቪ ብቁ ለመሆን ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሊኖርዎት ይገባል።
    - የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ የመልቀቂያ ፈተና ወስደው ቢያንስ በአምስት የትምህርት ዓይነቶች የማለፍያ ውጤቶች (ማለትም ከA እስከ D) ወይም፣
    - የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ማጣሪያ ሰርተፊኬት፣
    - 10ኛ ክፍል አጠናቅቆ ሶስት ዓመት በሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤት ወይም በአንድ የትምህርት መስክ የሰለጠኑ መሆን፣ ወይም
    - ከኢትዮጵያ ወታደራዊ ት/ቤት መመረቅ፤

- <u>የሥራ ልምድ</u>:- ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የትምህርት ደረጃዎች የማያሟሉ (ሰዎች) ተገቢ የስራ ልምድ ሊታይላቸው ይችላል። ተገቢ የሥራ ልምድ ማለት፣ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት፣ የሁለት ዓመት የኮሌጅ ስልጠና ወይም የስራ ልምድ በሚጠይቅ የስራ መስክ በሙሉ ሰአት ሰራተኛነት መስራት ነው። **ከዚህ በላይ የተገለጸው የትምህርት ደረጃ ወይም በአሜሪካ የሥራ ሚኒስቴር የሙያዊ ክህሎት ዝርዝር መሠረት የሁለት ዓመት ተገቢ የስራ ልምድ ከሌለዎት አያመልክቱ።** የአሜሪካ የሥራ ሚኒስቴር የሙያዊ ክህሎት ዝርዝር በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ-ገጽ http://online.onetcenter.org ላይ ይገኛል።

- **ኢ-ሜይል**፡- በ2011 □ቪ ሉተሪ ም□□ባ ወቅት የኢሜል አድራሻ መካተት አለበት፡፡ የአሜሪካ መንግስት በምንም ዓይነት የዲቪ አሸናፊ መሆንዎን በኢ-ሜይል አያበስርም፡፡ አሸናፊ መሆንዎ ከአሜሪካ መንግስት የሚደርስዎት በፖስታ መልዕክት ብቻ ነው፡፡ አሸናፊ መሆንዎ በፖስታ ከተገለጸሎት በኋላ ግን ጉዳይዎ የደረሰበትን ለመከታተል የአሜሪካ መንግስት ኢ-ሜይል ሊልክልዎት ይችላል፡፡ በምንም አይነት የገንዘብ ክፍያን የሚያካትት መልእክት በኢሜል አድራሻዎ አይላክሎትም፡፡ የዲቪ አሸናፊ መሆንዎን የሚያበስር ወይንም የገንዘብ ክፍያን የሚጠይቁ የኢሜል መልእክቶች ሁሉ የተጭበረበሩ መሆናቸውን ያሰተውሉ፡፡

- **ሰነዶች**፡- የተጭበረበሩ ሰነዶችን ለአሜሪካ ኤምባሲ አያቅርቡ፡፡ የተጭበረበሩ ሰነዶች ማቅረብ በቀጥታ ማመልከቻዎትን ውድቅ ያስደርገዋል፡፡

- ***ቃለ-መጠይቅ***፡- የተመረጡ ከሆነ፣ ለቆንስላው ቃለ-መጠይቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ሰነዶች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያልተዘጋጁ ሰነዶችዎን በሙሉ የግድ ወደ እንግሊዝኛ ማስተርጎም ይኖርብዎታል፡፡

***ማቅረብ የሚጠበቅብዎ ሰነዶች***፡

- ፓስፖርት
- የልደት የምስክር ወረቀት
- የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ባለትዳር ከሆኑ)
- የፍቺ የምስክር ወረቀት (አግብተው ከተፋቱ)
- (ከወንጀል ነጻ መሆንዎን የሚያረጋግጥ) የፖሊስ የምስክር ወረቀት
- (አመልካቹ እድሜው 16 እና ከዚያ በላይ ከሆነው በኂላ ዜግነት ካገኘበት የትውልድ አገሩ ወጥቶ ከ12 ወራት በላይ ከቆየ) ከቆየበት አገር (ከወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ) የፖሊስ የምስክር ወረቀት፣
- ከአገር የማባረሪያ ወረቀት (ከቆዩበት አገር የተባረሩ ከሆነ)
- የፍርድ ቤት እና የወህኒ ቤት ሰነድ (የሚመለከትዎት ከሆነ)
- ወታደራዊ መዝገብ (የሚመለከትዎት ከሆነ)
- የትምህርት ማስረጃ (በብሔራዊ የፈተናዎች ድርጅት የተረጋገጠ) ወይም የስራ ልምድ ማረጋገጫ
- ሙሉ የፊት ገጽን የሚያሳይ ፎቶግራፍ (50ሚሊሜትር x 50 ሚሊሜትር)

ለዲቪ ስራ ማስኬጃ እና ለማመልከቻ ክፍያ 755 የአሜሪካ ዶላር